# የኢንተርሃሙዌው “የዋጭ ዋጭ” ግበረሃይሉ ጫጫታ!

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ)

ክፍል (2)

“ዋጭ ዋጭ” ትግርኛ ነው።አማርኛው “ጫጫታ ትርምስ”። በእንግሊዙ “ከያስ ወ አናርኪ”።
ኢነተርሃሙዌስ ምን ማለት ነው? Interahamwe፤-ማለት ሑቱ የተባለው ሚሊሺያ በ1994 በሩዋንዳ የተካሄደው የዘር ማጥፋት/ጀነሳይድ ወንጀል የፈጸመው “የተደራጀ የነብሰ ገዳይ ግበረሃይል ነው”።

“According to the ICTR, the term Interahamwe derives from two words intera and hamwe. Intera comes from the verb 'gutera' which can mean to attack, to work or to kill. 'Hamwe' means together. Therefore Interahamwe could mean to attack or to work together, and, depending on the context, to kill together. The Interahamwe were a youth movement. During the war, the term also covered anyone who had anti-Tutsi tendencies, irrespective of their political background.”





ከጦቢያው ጸጋዬ ገብረመድህን ልዋስ እና ትችቴን በዚህ ልጀምር መሰለኝ። Oysters የተባለ እንሰሳት በጠፌ ጨረቃ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ይከፈታል ይባላል። Crab የተባለው እንሰሳ (አብዛኛው ዓለም ይበላዋል) አይስተሩን ሲያይ ትንሽ ድንጋይ  ወይም የባሕር አረም (አራሙቻ) ይወረውርበታል። አይሰተሩ እንደገና

ራሱን መዝጋት



ያቅተዋል። የክራቡ ምግብም ይሆናል። አፉን በጣም በመክፈት ራሱ ላይ ከፍተኛ ችግር ሚያደርስ ሰውም ዕጣ ይኸው ነው። ዲያስፖራ የመሸገው ኢትዮጵያዊ ኢንተርሃሙዌው "የዋጭ ዋጭ" ግብረሃይል ቡደኑም" ዕጣ ፈንታው የአይስተሩ ዕጣ ይሆናል።

ኢንተርሃሙዌው በጌታቸው ረዳ ላይ ሲዘምት ሰንብቷል። ሊዘምት ያነሳሳው ምክንያት የጌታቸው ረዳ መነጽር የፈተሸው የአንዳርጋቸው ጽጌ የታሪክ ማሕደር መነሻ የሚከተለው ስለዘገበ ነው። "በዋናው ቁም ነገር ላይ ስናተኩር የአገሪቱ ምስረታ በዋንኛነት ያውም በአንድ ክልል በሚገኝ የሸዋ አማራ መሳፍንት የሃይል እርምጃ የተከናወነ ነበር።" አንዳርጋቸው ጽጌ (የአማራ ሕዘብ ኬት ወዴት ገጽ 9) "ኢትዮጵያ ብሄሮች በባርነት ሰንሰለት የታሰሩባት አገር ናት ገጽ 11) **(ከእኛው ከአማሮቹ መካካል ጥቂቶቹ ዜግነቱ ሲጠየቅ "ኢትዮጵያዊ" ነኝ የሚል "ብሔሩ ጠፍቶት" ሳይሆን "ስልጣን እና ጥቅሙን ለማቆየት ብቸኛው መንገድ ይህ ብቻ ነው ከሚል ንቃት/ተንኮል የመጣ ነው"** አንዳርጋቸው ጽጌ የአማራ ሕዝብ ከዬት ወዴት- ገጽ 24) "አንዳርጋቸው ባንዳ ነው ባንዳ አይደለም?" የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራ ናዚ ኔት ዎርኮች በትግራይ ሕዘብ ላይ የሚያስተጋቡት ዛቻ" አንዳርጋቸው ጽጌ በወያኔ እጅ ከገባ በኋላ በኢትዬጵያን ሰማይ ድረገጽ የቀረቡ ከላይ የተዘረዘሩት ትችቶች መነሻ ያደረገ ነው።

እዚህ ውጭ አገር ብቻ ለ22 አመት ያህል ወያኔን ስቃወም፤ ጀሮዬ ያዳመጠው በትግራይ ሕዝብ ላይ 'ካንሰር" የሚል ስም ከብዙ አመት በፊት በአንድ ምሁር አንደበት አንደተጀመረ አስታውሳለሁ።

ከዚያም በመቀጠል፤ አርበኞች ግምባር የሚባል ድርጅት ኦክላንድ ከተማ ካሊፎርኒያ ክ/ሃገር ተመስርቶ በሕገ ደምቡ ላይ "ከትግሬ ጋር መጋባት የተከለከለ ነው" የሚለውን አንቀጽ አንዳሰፈረ አንድ የትግሬ ታዋቂ ምሁር ወዳጄ ከወደ አውሮጳ አንድመለከተው ልኰልኝ በመጽሐፌ ላይ አስፍሬዋለሁ።

ያንን ስመለከት ማመን ነበር ያቃተኝ። ቀጥሎም "የኦሮሞ ነፃነት ግምባር / ኦ ኤል ኤፍ/" የተባለው ቡድን ጀሌዎቹ ፓል ቶክ ተብሎ የሚታወቀው ማሕበራዊ የመነጋገርያ የኢንተርኔት መድረክ በተከፈተ ከጥቂት ሳምንታት ቆይታ ልምምድ በኋላ "በአማራው ማሕበረሰብ" ላይ የዘር ማጥፋት ዘመቻ በመክፈት

“የአማራን ቆዳ ስልቻ አድርገን የውሃ መቋጠሪያ ወይንም የእህል መያዣ እናደርገዋለን” የሚል በጣም ዘግናኝ የኢንተርሃሙዌ ዛቻ እና ቅስቀሳ አደረገ። ተቀዳው ድምፅ አሁንም ከኔው ጋር አለ።

እሱን ተከትሎ ኦፓልቶኩን አደ ማሕበራዊ ድረገፆች እየተስፋፋ እና ሕዝቡም ሲለማመደው፤ “ኢካዴፍ/ካረንት አፌርስ/ECADF” የተባለው የፓል ቶክ እና ድረገጽ መድረክ “ከትግሬ ጋር እንዳትጋቡ፤ አንኳን ለጋብቻ ለጓደኝነትም እንዳትፈልጓቸው፤የተጋባችሁ ምንም ማድረግ አይቻልም፤ ከዛሬ ጀምሮ ግን ትግሬ ከሚባል አንዳትጋቡ አንዳታስጠጉ፤ አንዳታምኑ…” በማለት በሰፊው በረዢም የታተተ የኢንተርሃሙዌው ቅስቀሳ በዛው ክፍል አዳመጥኩኝ (አውዴዮው ከኔ ጋር አለ (ኢትዮፕያ ፈረሰት/ቤን በሚባለው የወያኔ ካድሬ በድሮ ድረ ገጹ ላይ ተለጥፎ አንደነበርም ይታወሳል)። ቀጥሎ በኢካዴፍ ፓል ቶክ በተከታታይ በአስተዳዳሪዎቹ እና በታዳሚዎቹ በኩል “ጸረ ትግሬ” የኢንተርሃሙዌው ደውል መቃጨል ቀጠለ።

የኢንተርሃሙዌው ቡድን እያዘገመ ሲያሰራጨው የነበረው ትግሬን የማጥፋት ዘመቻ በ2012 ፈረንጅ ዘመን ደግሞ የሚከተለው “አስፈሪ” ዛቻ ተሰራጨ። ሚካኤል ንዋይ ይባላል። ወጣት ነው። በትግሬዎች እና በኤርትራኖች ላይ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ጥሪ አስተጋባ። ልጁ የካረንት አፌርስ (ECADF)ጉልት ነው።ከዚያ ከእናት ክፍሉ ውስጥ አይጠፋም። በሚከተለው የተዘጋ ቪድዮ የምታዩት ሚካኤል-ንዋይ ይባላል። ወጣቱwww.saveshewa.org የሚባል ኢንተርኔት/ድረገጽ አለው/ነበረው።ሚካኤል-ንዋይ ያስተላለፈው በትግርኛ ተናጋሪ ሕብረተሰብ የዘር ማጥፋት ጥሪ ያስተላለፈው ይኼው፡ እዚህ ይጫኑ www.youtube.com/watch?v=wxwguLrEu4w&feature=youtube_gdata_player ቪድዮው “ከፍርሃት የተነሳ” ይመስለኛል “ፕራይቬት” ስለሚል ማየት አትችሉም። በወቅቱ ግን ብዙ ሰው አይቶታል። በሌላ የቪድዮ ፎርማት በፋይል ከጓዶቼ ጋር ተይዟል። ሆኖም ሌላ ቀን አቀርብላችኋለሁ።

አድብቶ የነበረው የኢንተርሃሙዌው ሌላው ቡድን ደግሞ “ኢትዮጵያ አውት ኦፍ ኦሮሚያ!” “አንገታቸውን በማቸት ነው የምንቀላው!” በማለት ተደብቆ ሲያደባ የነበረው አደገኛ የኢንተርሃሙዌው ቡድን እስልምና እና የኦሮሞን ጉሳ ደበላልቆ አንድ ነህ በማለት ሃይማኖት ተንተርሶ የሚያቃጭል ሌላ የኢንተርሃሙዌ ቡድን ተከሰተ።


የማቼት እና የጐራዴው አብዬት ብዙውን ሰው ከመቀመጫው አስነስቶ ካስደነበረው በኋላ፤ እያነከሰ ፤ዝግ እያለ እንደ ጅብ ተደብቆ የነበረው ሌላው “ኢንተርሃሙዌው የጫው ጫው ግብረሃይል” ቡድን ደግሞ ወቅቱን ጠብቆ “አርበኛዬ/መመኪያ” ሲለው የነበረው “አንዳርጋቸው ጽጌ” በወያኔ እጅ መውደቁን ሲሰማ “ካንሰሩ፤ ቅማላሙ እና አምበጣ በሊታው የትግሬ ሕብረተሰብ ላንዴ እና ለመጨረሻ ከምድረገጽ ፈልገን በያለበት ማጥፋት ወይንም ማግለል አለብን” በማለት “Tigray and Tigrayans are terminal cancer to Ethiopia and Ethiopians.... ban and isolate from any social participation in any Diaspora community” በማለት ‘ትግራይ የሚባል መሬት እና ሕዝብ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያኖች ነቀርሳ ስለሆኑ ከማንኛውም ውጭ አገር በሚገኙ ማንኛቸውም ማሕበራዊ ግንኙነት መገለል እና መወገድ አለባቸው!” በማለት ተደብቆ ሲያነክስ የነበረው የኢንተርሃሙዌው ቡድን በሩ እና ጐዳናው፤ ጠበሉ፤ ቤተክርስትያኑ እና መስጊዱ፤መዝናኛዎች፤ በዓላቱ እና ማሕበራዊ ግንኙነቶች በሙሉ ለትግሬዎች አንዲከረቸም በየፓልቶኩ አወጀ። በየቀኑ ያለ ማቋረጥ “ኦይስተራዊው አፉን” እስኪቀደድ ድረስ ተከፈተ። በተደራጀ መልኩ በፓልቶክ አስተዳዳሪዎች መሪነት “ነቀርሰውን” የማግለል ቅስቀሳ ተዘረጋ። አሎሄ!!

**’ኦይስተሩ’ ኢንተርሃሙዌው በተከፈተው አፉ ላይ** **<u>“የዲያስፖራ ኢትዮጵያዊያን “ናዚ ኔት ዎርኰች” በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚያስተጋቡት ዛቻ”</u>** የሚል “ጠጠር” አፉ ላይ ወርውሬ መዝጋት ስለነበረብኝ ጭንቅላቱ አንደተረገጠ እባብ “የዋጭ ዋጭ ኡኡታው!” አስተጋባ ። በዚህም “ቅቤ አጠጣኸን” እና “ኰሶ አጠጣኸን” ያሉኝ ሁለት የተለያዩ የኢመይል እና የስልክ መልዕክቶች ደርሰውኛል። በጣም መረረን ያሉኝም የፈውስ ጣፋጭ የለም እና “በማር ለውሰው እንዲጋቱት” ምክሬን ሰጠሁ።

“የኢንተርሃሙዌው “ዋጭ ዋጭ” ግበረሃይሉ ቡድን” በብርቱካን መዲቅሳ ባለቤትነት የተመዘገበው “ቃሌ” የተባለው የፓል ቶኩ ክፍል ዋና አስተዳዳሪው “ታየ ሙሉጌታ” (ማጨው) ጌታቸው ረዳ “ናዚ ነው አለኝ” እያለ ያልተባለውን በገዛ እራሱ እሳት ላይ እግሩን ጥዶ ሲዘል ሲፈርጥ በራሱ ከልፍል ሲያስተጋባው የነበረው “ጫው ጫው” እና ቃሌ ፍረድ ቤት ችሎት በሌለሁበት የተፈረደብኝን ፍርድ ላውጋችሁ።

“ሰለሞን 2” በሚል የፓል ቶክ መጠሪያው በቃሌ የቀበሌ የፍረድ ቤት ዙፋን ተቀምጧል። 113 ሰው ክፍሉ ላይ ታጭቋል። “እስኪ እጃችሁን አንዳንድ በማውጣት 1 1 በሉኝ እና ጌታቸው ረዳ “ወንጀለኛ” ነው የምትሉ አሳዩኝ በማለት ክፈሉ አንዳለ 1 1 በማሳየት “ቃሌ” በተባለው የከፍተኛ 11 ፍርድቤት በዋለው ችሎት “ወንጀለኛ” ብሎኛል። ወንጀለኛ ደግሞ “ለግድያ ወይንም ለእስራት” ቅጣት ይዳረጋል ማለት ነው። የደርግ እና የማኦይስቶች ፍርድቤት በሚመስል መልኩ “በቃሌ የፓል ቶክ ፍረድቤት” ላይ እጅ በማውጣት በዜጎች ላይ የሚፈረድ ውሳኔ ያስተላለፈልኝ ብይን “ታድኖ አንዲያዝ እና ‘ቃሌ ማጐርያ እስርቤት’

እንዲታሰር ወይንም ባለበት “ነፃ እርምጃ እንዲወሰደበት” የሚል ውሳኔ ገና እየጠበቅኩኝ ነው! ምናልባት ባለቤቱ የሆኑት ብርቱካን ሚደቅሳ “እንደወንጀለኛ” ይግባኝ ብዬ እንደ ሥዬ አብርሃ በዋስ ይለቁኝ ይሁን አይሁን ብይኑ ከተሰጠኝ በኋላ አስታውቃችኋለሁ። በአቶ “ሰለሞን 2” ዳኝነት የተመራው ክቡር ፍረድቤቱ በምኖርበት ከተማ ድረስ “ነፃ እርምጃ” የሚወስዱ “ገዳይ ስኳዶቹን” በመላክ ውሳኔ አስተላልፎ “ካልገደለኝ” በዚህ ጉዳይ ብርቱኳን መዲቅሳ ቤታቸው እንዲቆጣጠሩ መልከቴን በአደራነት አስተላልፋለሁ። This room is owned by Birtukan Mediksa የሚል በባለቤትነት ስም ተጽፎ በክፍሉ አናት ላይ ተጽፎ የሚነበብ የባለቤትንት ምዝገባ ስለሚታይ ማለቴ ነው። ለሁሉም “ምቅናይ ጽቡቕ”! እንዳለው ዘፋኙ ኪሮስ አለማዬህ “መሰንበት ደጉ!” ስንሰነብት “የጫው ጫው ፍ/ቤቱ ቡድን” ውሳኔ በሰፊው እንከታተለዋለን። በጸረ ትግሬነታቸው የታወቁት እነ “ቂጣ ራስ” የተባለች ወጣት ሴት የዋሉበት የተከበረው የፓልቶክ የቃሌ ፍረድ ቤት በጌታቸው ረዳ ላይ 1 1 ምልክተ በማሳየት ውሳኔውን ሲያስተላልፍ በዜና ቀራጮች ለታሪክ ተዘግቦ የሚቀር ኢመጅ ይኼው ከዚህ በታች ያለውን ትክክለኛ ቅጅ ይመልከቱ፡




የዘመናችን አሉላ አባ ነጋ ተብሎ የተቃኘለት ዝነኛው ወዳጄ ገብረመድህን አርአያም ከኢንተርሃሙዌው ሰይፍ አላመለጠም። “ራስ ዳሸን” በማለት እራሱን በሚጠራ የፓል ቶክ ኢንተርሃሙዌው ቡድንም “ሕልሜ በሕይወት እያለሁ አንድ ትግሬ ገድዬ መሞት ነው ዓላማዬ” በማለት በማንም ትግሬ ላይ የግድያ ዛቻ ያስተላለፈው አንድ የወልቃይት ሰው ነኝ የሚል “የኢንተርሃሙዌው አባል” ፤ “ራስ ዳሸን” ብሎ ራሱን በሚጣራ “ማሞ ቂሉ” የሆነ ሰው ያንድ አካባቢ መሆናቸውና ከወልቃይቴው ሰው እንደሚተዋወቁ “ስም እና አድራሻውም” በፓልቶክ ክፍል ቀርቦ ሲነግረን እኔ በጣም ነበር የደነገጥኩት። “ራስ ዳሸን” ንግግሩን በመቀጠል “ጌታቸው ረዳ እና ገብረመድህን አርአያ.....አረጋዊ በርሄ.....ወዘተ.....ወዘተ,,”ሁሉም የሚታመኑ ትግሬዎች ስላልሆኑ ወልቃይቴው ትግሬን እገላለሁ ቢል አትፍረዱበት በማለት በእኛ ላይ ግድያ ቢፈጸም ደስተኛ እንደሆነ “ራስ ዳሸን” ገልጿል። የኢንተርሃሜው ቡድን ገብረመደህን አርአያንም ጭምር አላተረፈውም። ጉድ ፈላ! ምቅናይ ፅቡቕ! ይህንን የጨለማ ግስጋሴ ማየት ያቃታቸው ዜጐች ነገሩን ቸላ በሉት “ሰካራሞች ናቸው” “ቁም ነገር አትቁጠሩት” እያሉ “የትግራይ ህፃናት እና ዘመዶቻችን አንገታቸው በካራ እስኪታረዱ ድረስ ቁጭ ብለን እንድንጠብቅ እያጃጃሉን ነው። ከሃያ አንድ አመት በፊት የአማራ ሕፃናት ልጆች ኢትዮጵያ ውስጥ በአደገኛው የኦሮሞው ኢንተርሃሙዌው ቡድን ሲታረዱ ሕዝባችን ናቸው ብለን እንደጮኽንላቸው ሁሉ፤የራሴ ነገድ ህዳጣን የሆነው የትግራይ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በእኔም ላይ ያነጣጠረ አደጋ ስለሆነ መጮሄን ያስከፋቸው ሰዎች ማዬቴ በጣም አሳዝኖኛል። ባለፋት ወራቶች 9 የትግሬ ሽቃዮች በካራ አንገታቸው ተቆርጠዋል። በእኛ እና በሕዝባችን እያነጣጠረ ያለው አደጋ ማሳወቅ የሚጠበቅብን ነው። ስለሆነም እራስችንን ለመከላከል ስንነሳ “ጠባቦች/ዘረኞች፤ ወየኔዎች ተብለናል”!



የዘመናችን አሉላ አባ ነጋ ገብረመደህን አርአያም ከኢንተርሃሙዌው የዋጭ ዋጭ ግብረሃይል ቡድን “ቆሻሻ ዘለፋ” አላመለጠም። ምቕናይ ፅቡቕ! መሰንበት ደጉ! ብዙ ያሳል። ናጎረሰኩኝ እጄ ተነከሰኩኝ። ከነሱ ጋር ሆነን በታገልን “ዘለፋ” አከናነቡን! የወያኔ እጅ መንሻ ሊያደርገን ነው! ጌታቸው ረዳ ወደ ዳዊት ከበደ እየሄደ ነው! አገር መግባቱ ነው! ይላል ቆሻሻው የኢንተርሃሙዌው ቀዳዳ አፍ። ትግሬን ለማጥፋት ከዛታችሁ “ወያኔን እድሜ ልካችሁ ይረገዛችኋል” ስንል፤ “ጌታቸው ረዳ ደብቅ ወያኔ ነው” እያለ ኢንተርሃሙዌው ሲያብድ ሲዘልል፤ ሲጮህ፤ሲቂቁነጠነጥ ሰነበተ። ያለ ትግሬ ሱታፌ “ወያኔ ይወገዳል” ፤ ያለ ትግሬ ኢትዮጵያ “ኢትዮጵያ” ትሆናለች የሚለው ኢንተርሃውሜው ቡድን መስከር ብቻ ሳይሆን “አብዷል’።

ወደ ሌላው አንሺጋገር። Ethiopian Current Affirs Discussion Forum (ECADF) (የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ) እና Ethiopian Free **Discussion Forum Voice Room** የተባለው የኢንተርሃሙዌ “የዋጭ ዋጩ” ግበረሃይሉ ቡዱን ደግሞ **ሰሞኑን ያለ ሟቋረጥ ለአንድ** ሳምንት አንደ “ሉሲፈር” ወደ ሰራቄ ሞት ተቀይሮ “በመጋዝ ጥርሱ” በምናሙ እየዋዠቀ ‘ስጋዬን ሲቦጭቅ፤ደሜን ሲጠጣ፤ ሲያኝከኝ፤ሲያነሳኝ፤ሲጥለኝ፤አጥንቴን እየቆጠረ ሲቆረጥመኝ፤ሲፈልጠኝ፤ አፍንጫን ምላሴን፤ ጆሮዬን እየዘለዘለ ሲያመነዥከው ሰነበተ”! ስሃሊነነ ቅዱስ! የህንን ሰው በሊታው የኢንተርሃሜው ቡድን ትግራይን እና ትግሬን ለማጥፋት “ትግሬ ትግሬ ነው! ካንሰር ካንሰር ነው! ከዝንጀሮ ማን ይመረጣል” እያለ ሲያመነዥከኝ አድምጩው ከጥቂት ወራት በፊት ኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ቤንሻንጉል አካባቢ ከመኪና ተጎትተተው የታረዱ 9 ምስኪን የትግራይ ሸቃይ ሰራተኞች አንገታቸው ሲቆረጥ ታየኝ እና “የዲያስፖራው ኢንተርሃሙዌው ቡድን” አገር አንዳይገባ ፤ጸሎቴን ወደ ፈጣሪ አደረስኩ።

የኢንተርሃሙዌው “የዋጭ ዋጭ” ግብረሃይሉ ክፍል ሰሞነኛው የዋጭ ዋጭ ውሎው ዘገባ በክፍል 3 ይቀጥላል። ጌታቸው ረዳ (editor Ethiopian Semay) getachre@aol.com